22 May 2010

# ማስታወቂያ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ አሜን።

የተከበራችሁ ምእመናን፤

ባለፈው ሳምንት ቤተክርስቲያናችን ለአምስተኛ ጊዜ መከሰሷን በአውደምህረት ቆመን አስታውቀናችሁ ነበር። በ5/18/2010 ዓ/ም በ101st. District Court በዋለው ችሎት በከሳሽ በኩል የነበሩ ምስክሮች

1. አቶ ግርማቸው አድማሴ
2. ወ/ሮ ሶፊያ ዘሪሁን
3. አቶ መስፍን ወልደየስ
4. ወ/ሮ የሺ ዘሪሁን ሲሆኑ

በተከሳሽ በኩል የነበሩ ምስክሮች ደግሞ

1. አቶ አበራ ፌጣ
2. አቶ ገብሬ ታደሰ
3. አቶ አገሬ ታደሰ
4. ዶ/ር ግርማ ወልደሩፋኤል ነበሩ።

እነዚህ ምስክሮች ከተደመጡ በኋላ ክቡር ፍርድ ቤቱ በቤተክርስቲያኗ ላይ የተደረጉት ማገጃዎች እንዲነሱና በከሳሾች በአቶ ተኮላ መኮንን እና በአቶ ጸሀይጽድቅ ቤተማርያም የተመሰረተው ክስ ደግሞ ቀደም ሲል በአቶ ዳግም ካሳሁን እና በወ/ሮ ጥሩ አየር ፍስሀ በቤተክርስቲያናችን ላይ የተመሰረተውን ክስ ውድቅ ወዳደረገው ወደ 192nd. (District court) ፍርድ ቤት እንዲዘዋወር (እንዲመለስ) ወስኗል። ይህም የተደረገበት ምክንያት የሁለቱ ክሶች ከሳሾች ስም ዝርዝር ይለያይ እንጂ ክሶቹ ተመሳሳይ ስለሆኑ ነው።

ቀደም ሲል ቤተክርስቲያኗ ለሕዝበ ክርስትያን የምትሰጠውን አግልግሎት ሲጠቀሙ እንደነበር ሁሉ አሁንም የቤተክርስቲያኗን ሰላምና ስነስርአት እስከጠበቁ ድረስ ከሳሾችም ሆኑ ደጋፊዎቻቸው ገብተው አምልኮተ እግዚአብሔር ሊያደርሱ የሚችሉ መሆናቸው በፍርድ ቤቱ ተገልጿል። የቤተክርስቲያኗን ሰላም ቢያደፈርሱ ግን የአስተዳደር ቦርድ ተወካይ ወይም አባል በሰላም ከቤተክርስቲያን እንዲወጡ ይጠይቃል፤አንወጣም ቢሉ ግን በህግ አስከባሪዎች ህጋዊ እርምጃ የመውሰድ መብቱ የተጠበቀ እንደሆነም ፍርድ ቤቱ ወስኗል። ይህንን ውሳኔ ለማየት የሚፈልግ ሁሉ ወደቤተክርስቲያኗ ድረ ገጽ (ዌብ ሳይት) www.stmichaeleoc.org በመሄድ መመልከት የሚችል መሆኑን እየገልጽን ይህንኑ በተመለከተ ተጨማሪ ጥይቄ ያላችሁ ቦርዱን በመጠየቅ ትክክለኛውን ግንዛቤ ማግኘት የምትችሉ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ እንገልጻለን።

እግዚአብሔር ቤተክርስቲያናችንን በሰላም ይጠብቅ።